# የጥልቅ ተሃድሶው ውጤት

# ነጸብራቆች

**ስሜነህ 05-29-18**

የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከነሃሴ 10-15/2008 ዓ.ም ድረስ ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ያለፉትን አስራ አምስት ዓመታት የለውጥ ጉዞ በመገምገም በአንድ በኩል በእስካሁኑ ትግል የተመዘገቡ ውጤቶችን አጠናክሮ ለመቀጠል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን የሚፈታተኑ ችግሮችን በመቅረፍ የህዝብ መብትና ተጠቃሚነትን ለማጎልበት የሚያስችሉ ውሳኔዎችን ማሳለፉ ይታወሳል፡፡

ከነዚህ ውሳኔዎች አንዱና ዋነኛው ልማታዊ መንግስት የመንግስትን ስልጣን የህዝብን ኑሮ ለማሻሻልና አገራዊ ለውጡን ለማስቀጠል የሚበጅ መርህና ርእዮት ሆኖ ሳለ አመራሩ ስልጣኑን ለውጡን ለማስቀጠል ከመጠቀም ይልቅ የግል ኑሮ መሰረት አድርጎ የመመልከትና በአንዳንዶችም ዘንድ የግል ጥቅም ከማስቀደም ጋር እየተያያዘ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የተሰጠው ውሳኔ ነው። ይህም እንዲህ ተገልጾ የነበረ መሆኑ ይታወሳል።

*አገራዊ ለውጡ በስኬት ሲጓዝ የቆየው መንግስታዊ ስልጣንን ለህዝብ ጥቅም ማስከበሪያ ማድረግ በመቻሉ የሆነውን ያህል ይህ ስልጣን ያለአግባብ ለመጠቀም ለሚሹ ግለሰቦች በመሳሪያነት ማገልገል ሲጀምር የተጀመረው ልማት ይደነቃቀፋል፡፡ መልካም አስተዳደርም ይጠፋል፡፡*

*በአሁኑ ጊዜ ህዝብን በማስመረር ላይ ያለው ችግር ዋነኛ መንስዔ ይህ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ደረጃውና መጠኑ ምንም ይሁን ምን የመንግስት ስልጣንን ካለ ያለአግባብ ለግል ኑሮ መሰረት ለማድረግ የሚታየው ዝንባሌና ስህተት መታረምና መገታት እንዳለበት፣ ይህን ለማድረግ*

*የሚያስችል ተጨማሪ እርምጃም መውሰድ እንዳለበት ወስኗል፡፡ ዝንባሌው በሚታይባቸው ቦታዎች ሁሉ በአግባቡ እየተፈተሸ እንዲስተካከልና የድርጅታችን ጥራትና ጥንካሬ ተጠብቆ እንዲቀጥል አስፈላጊ የሆነው ርምጃ ሁሉ እንዲወሰድ ወስኗል፡፡ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በዚህ ረገድ ከራሱ ጀምሮ የሚታዩ የጥገኝነት አስተሳሰቦችና መገለጫ የሆኑትን ጠባብነትና ትምክህተኝነትነ እንዲሁም የጥገኝነት ተግባራትን በጥብቅ በመታገል ይህ አዝማሚያ እንዲገታ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር ዕቅዶችም አዘጋጅቷል፡፡*

ስለሆነም ኢህአዴግ ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ከገጠሙት ከባድ ፈተናዎች ሁሉ ዋነኛ የሆነው መንግስታዊ ስልጣን በእጁ ከመግባቱ ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ የሚያጠይቁ እርምጃዎች አሁን የጥልቅ ተሃድሶው ውጤት በሆኑት የግንባሩ ሊቀ መንበርና የኢፌደሪ ጠቅላይ ሚንስትር እየተወሰደ ነው።የመንግስት ስልጣንን መያዝ በአቋራጭ ለመክበር እጅግ የተመቸ ሆኖ መገኘቱን በግምገማው አንጥሮ ያወጣው ኢህአዴግ በየደረጃው እርምጃ መውሰዱን ቀጥሏል። መንግሥታዊ ሥልጣንን ብዙኀኑን የበይ ተመልካችነት ማረጋገጫ አደርጎ ለመጠቀም የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ የድህነትን አዙሪት በማባባስ አገሮችን ወደ ቀውስ እንደሚያመራ የተሟላ ግንዛቤ ያዳበረ ድርጅት መሆኑና በዚህ ግንዛቤ ላይ በመመስረት የመንግስት ስልጣን ሀብት የመቀራመቻ ሳይሆን የብዙኀኑን ሀብት የመፍጠርና የመጠቀም ብቃት የመገንቢያ መሳሪያ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን እየወሰደ ነው። ከእነዚህ እርምጃዎች መካከልም የጥልቅ ተሃድሶው ውጤት የሆኑት አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ስልጣናቸውን የህዝብ ሃብት መቀራመቻ ያደረጉ ሃይሎችን በውጭ ያለ ሂሳብ ማስመርመር መጀመራቸው የሚጠቀስ እና መሰረታዊ የሆነው እርምጃ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር) ማክሰኞ ግንቦት 7 ቀን 2010 ዓ.ም. በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ከሚኒስትሮች፣ ከሚኒስትር ዴኤታዎችና ከዋና ዳይሬክተሮች ጋር ባደረጉት ውይይት፣ ይህን እርምጃ ይፋ ከማድረጋቸውም በላይ አሁን ያለው የመንግሥት አሠራር እንደማያዋጣና እያንዳንዱ የሥራ ኃላፊ አሠራሩን በመፈተሽ ማሻሻያዎችን እንዲያደርግ ማሳሰቢያም ጭምር መስጠታቸው ከላይ የተመለከተው የጥልቅ ተሃድሶው ውጤት ነጸብራቅ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጠንካራ ቃላት በተሞላው ንግግራቸው፣ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የሚጎድሏቸውና አሁን መንግሥት ላለበት ሁኔታ በአጣዳፊነት መፍትሔ ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ይህና የህዝብ ሃብትን ማስመለስ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አገሪቱ አድጋለች ከማለት በዘለለ የሕዝቡ ቀጥተኛ ተጠቃሚነት ምን እንደሚመስል በሚያሳይ ደረጃ መለካት እንደሚኖርበት ባሳሰቡበት በዚህ መድረክ፤ ካሁን በኋላ የካቢኔ አባላት ቆይታ የሚወሰነው በአፈጻጸም ላይ ተመርኩዞ እንደሚሆን አረጋግጠዋል። እያንዳንዱ ሚኒስትር ከሚቆጣጠረው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ጋር የሥራ ውል በመግባት ሥራን ቆጥሮ ተረክቦ፣ ቆጥሮ የማስረከብ አሠራር ለማሥፈን ከመስከረም ወር ጀምሮ ወደ ተግባር እንደሚገባም አስታውቀው፤በተለያዩ የውጭ አገር ባንኮች አካውንት ያላቸው ባለሥልጣናት መንግሥት መረጃው እንዳለው፣ በውጭ መንግሥታት ትብብር በአካውንታቸው ላይ ምርመራ እያደረገ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ይህን ተከትሎ ታዲያ በተጭበረበሩ የማስያዣ ንብረቶችን ጨምሮ በተለያዩ መጠቃቀሚያዎች ከሃገር ውስጥ ባንኮች በብድር የተመዘገቡ ሂሳቦችም እንዲጣሩ እና ወደመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆኑ ህዝብ እያነሳ ነውና በዚህ አጋጣሚ ለጠቅላይ ሚንስትሩ ማስታወስ ተገቢ ይሆናል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አዲሱ ካቢኔያቸውን አደራጅተው በሙሉ ኃይል ሥራ ሲጀምሩ በማስጠንቀቂያ ጭምር ውጤት እንደሚፈልጉ ከላይ በተመለከተው መልኩ የተናገሩትም ከላይ ስለተመለከተው የጥልቅ ተሃድሶው ውጤትና የዚሁ ውጤት ስለሆኑት ቀይ መስመሮቻቸው ነው፡፡ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ፌዴራል መንግሥቱ መዋቅር ውስጥ ያለው የሥራ ባህልና ዝርክርክርነት ይታወቃል፡፡ ስለሆነም የሂሳብ ምርመራውም ሆነ እርምጃው በተሃድሶው ልክ እስከታች መውረድ አለበት የሚሉ ዜጎች ይህን እውነት ስለሚያውቁት ነው። በእርግጥ ትልቁ ተሃድሶም ይህንኑ እውነት የደረሰበት መሆኑም ተገልጿል።

በዶክተር አብይ የተሾሙት አዲሶቹም ሆኑ ከቦታ ወደ ቦታ የተዘዋወሩት ወይም ባሉበት የሚቀጥሉት፣ ይኼንን አስመራሪ ቢሮክራሲ እንዲያስተካክሉ ሃላፊነት የወደቀባቸው እንደሆነም ማስጠንቀቂያ አዘል ከሆነው የጠቅላይ ሚንስትሩ ማሳሰቢያ መገንዘብ አይከብድምና የሚጠበቅ ይሆናል።የጠቅላይ ሚንስትሩ ከላይ የተመለከቱ እና እዚህ ያልተገለጹ ማሳሰቢያዎች ተግባራዊ መሆን የሚችሉት ፣ ከፍተኛ የአገልጋይነት መንፈስና ብቃት ያላቸው ተሿሚዎች ሲኖሩ ነው፡፡ ይኼንንም ከግምት በማስገባት በፍጥነት ዕርምጃ መውሰድ ካልተቻለ ልፋቱ ሁሉ ታጥቦ ጭቃ ይሆናልና ነው የሂሳብ ምርመራው ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ጠቅላይ ሚንስትሩ በጀመሩት አግባብ በየደረጃው የሚሾሙ ባለስልጣናትም  በሕዝብ ውስጥ መግባባት የሚፈጥር ዕርምጃ በመውሰድ ማስተካከያ ማድረግ የሚችሉት፣ ልክ እንደእርሳቸው የሕዝብ አስተያየትን ማዳመጥ እስከቻሉ ብቻ ነው፡፡ ሕዝብ ጊዜ ሰጥቶ ውጤት ሲጠብቅ ‹‹የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል›› የሚለውን ዕድሜ ጠገብ ምሳሌን እያስታወሰ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ይህ ወቅት ዘና ብለው የተለመደውን ዓይነት አዝጋሚ ጉዞ የሚያደርጉበት ሳይሆን፣ በብርሃን ፍጥነት የሚወነጨፉበት እንደሆነም ጠቅላይ ሚንስትሩ አረጋግጠዋል።

እስካሁን አገሪቱን ችግር ውስጥ ከከተቱ መሠረታዊ ችግሮች መካከል አንዱ ይህና ስልጣንን የህዝብ ሃብት መቀራመቻ ከማድረግ ጋር የተያያዘው  ነው፡፡ አገሪቱ ላለፉት ሦስት ዓመታት ከገባችበት የፖለቲካ ቀውስ ለመላቀቅ ገና እንፉቅቅ ላይ ናት፡፡ የውጭ ምንዛሪ እጥረቱ በፈጠረው ችግር ምክንያት ኢኮኖሚው እየተንገዳገደ ነው፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ በእነዚህ ምርመራ በሚደረግባቸው ሌቦች አማካኝነት ነው። የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ እያገረሸ ባለው የዋጋ ግሽበት ምክንያት የተንሳቆለው በነዚሁ ሌቦች አማካኝነት መሆኑም ላይ ጥልቅ ተሃድሶው አንጥሮታልና እርምጃው ተገቢና ድጋፍ የሚያሻው ነው፡፡

በእነዚህ ሌቦች ከርሳምነት የተነሳ ዛሬ በመኖሪያ ቤት ዕጦት የሚንከራተቱ ሚሊዮኖች ናቸው፡፡ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ የሚሊዮኖች አኗኗር ያሳቅቃል፡፡ ኢፍትሐዊነትና ሌብነት ላይ በዚህ አግባብ የሆነ እርምጃ እስካልተወሰደ ድረስ አሁንም የአገር በሽታ መሆናቸው ይቀጥላል፡፡ ሌብነት ሄዶ ሄዶ ሰብዓዊ መብቶችንም ያሳጣል።  ዴሞክራሲያዊ መብቶችም የሚጨፈለቁት ለነዚሁ ሌቦች የዘረፉ መንገዱን ለማመቻቸት ነው።  የዜግነት መብቶቻቸው ተሚልተውላቸው አገራቸውን ለማገልገል የሚፈልጉ የመኖራቸውን ያህል፤ የነገው ብሩህ ሕይወት የሚታየቸው እንዳሉ ሁሉ፣ የሌቦቹ ቀጥተኛ ሰለባ የሆኑ ድሆች ደግሞ ነገን አጨልመው ቢያዩ ሊገርም አይገባም፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ ውጥንቅጥ ውስጥ ያለች አገርን ከማጥ ውስጥ ለማውጣት ብርቱ ትግል ማድረግ ይገባል። ይህም የሚረጋገጠው በጋራ ጉዳዮች ተስማምቶ እጅ ለእጅ በመያያዝ የጥልቅ ታሃድሶው ውጤት ነጸብራቅ ለሆኑት የጠቅላይ ሚንስትሩ እርምጃዎች ድጋፍ ማድረግ  ሲቻል ብቻ ነው፡፡ መጠነ ሰፊ ፅዳት እና የሂሳብ ምርመራ የሚያስፈልጋቸው የዛጉ መንግሥታዊ ተቋማት እና  ባለስልጣናት  ብዙ ናቸው፡፡ ግልጽነትና ተጠያቂነት ጠፍቶ የዘረፉ ምሽግ የሆኑም ብዙ ናቸው፡፡ ሲቪል ሰርቪሱም ሆነ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በብልሹ አሠራሮች ተዘፍቀዋል፡፡ የሠራተኞች የሥራ ሞራል የጠፋባቸውም ሆኑ በአገርና በሕዝብ ላይ ኪሳራ እያደረሱ ያሉ የመንግሥት ተቋማት መፅዳት የሚችሉት፣ በጥገና ሳይሆን  ጠቅላይ ሚንስትሩ በጀመሩት

አይነት በመሠረታዊ ለውጥ ነው፡፡ ይኼ መሠረታዊ ለውጥ መምጣት የሚችለው አቅምና ብቃት ከሥነ ምግባር ጋር ባጣመሩ ትጉኃን ሹመኞችም እንጂ በእርሳቸው ብቻ እንዳልሆነ ግን ሁሉም ሊገነዘብ ይገባል።እነኚህ ሹመኞች በለውጥ ውስጥ ያለች አገር አዳዲስ ፊቶችም ስለሚያስፈልጓት በጠቅላይ ሚንስትሩ መሰየማቸውን ለአፍታም ሊዘነጉ አይገባም ፡፡